የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያኛ ዓመት ቁጥር ፳፮
አዲስ አበባ የካቲት ፳ ቀን ፪ሺ፮ ዓ.ም.

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

20th Year No. 26
ADDIS ABABA 27th February, 2014


## ማውጫ


ደንብ ቁጥር ፫፻፬/፪ሺ፮ ዓ.ም.

ብሔራዊ የቆላ ዝንብና የገንዲ በሽታ መቆጣጠሪያና ማጥፊያ ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ........ ገጽ ፯ሺ፪፻፺


## CONTENTS


**Regulation No. 304/2013**

National Institute for Control and Eradication of Tsetse Fly and Trypanosomosis Council of Ministers Regulation........ Page 7290


## የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፫፻፬/፪ሺ፮

### ብሔራዊ የቆላ ዝንብና የገንዲ በሽታ መቆጣጠሪያና ማጥፊያ ኢንስቲትዩትን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፮፻፺፩/፪ሺ፪ (በአዋጅ ቁጥር ፰፻፫/፪ሺ፭ እንደተሻሻለ) አንቀጽ ፭ እና አንቀጽ ፴፭ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "ብሔራዊ የቆላ ዝንብና የገንዲ በሽታ መቆጣጠሪያና ማጥፊያ ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፫፻፬/፪ሺ፮" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፦

፩/ "የቆላ ዝንብ" ማለት የእንስሳት ደም ብቻ የሚመገብና የገንዲ በሽታ ህዋስን ከእንስሳ ወደ እንስሳ የሚያስተላልፍ ነፍሳት ነው፤

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION No. 304/2013

### COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF THE NATIONAL INSTITUTE FOR CONTROL AND ERADICATION OF TSETSE FLY AND TRYPANOSOMOSIS

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 and Article 35 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 691/2010 (as amended by Proclamation No. 803/2013).

1. **Short Title**

This Regulation may be cited as the "National Institute for Control and Eradication of Tsetse Fly and Trypanosomosis Council of Ministers Regulation No. 304/2013."

2. **Definitions**

In this Regulation unless the context otherwise requires:

1/ "tsetse fly" means an obligatory blood-feeding insect which transmits trypanosomosis from one animal to another animal;


ያንዱ ዋጋ Unit Price 4:00

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፹ሺ፩
Negarit Gazette P.O.box 80,001

፪/ "እንስሳ" ማለት ማንኛውም የቤት ወይም የዱር እንስሳ ነው፤

፫/ "የገንዲ በሽታ" ማለት በደም ውስጥ በሚኖሩ ጥገኛ ተህዋስያን የሚመጣ በሽታ ነው፤

፬/ "ተህዋስ" ማለት የገንዲ በሽታ መንስዔ የሆነ ባለ አንድ ህዋስ የደም ውስጥ ጥገኛ ወይም ፕሮቶዞዋ ነው፤

፭/ "የገንዲ መድኃኒት" ማለት የገንዲ በሽታን ለማከም ወይም ለመከላከል ጥቅም ላይ የሚውል ንጥረ ነገር ወይም የንጥረ ነገሮች ውሁድ ነው፤

፮/ "ባዮሎጂካል" ማለት ለላብራቶሪ ምርመራና ለቆላ ዝንብ እርባታ አገልግሎት የሚውል ሪኤጀንት፣ የዝንብ ዘርና የእንስሳ ደምን ያጠቃልላል፤

፯/ "ቴክኖሎጂ" ማለት የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታን ለመቆጣጠርና ለማጥፋት ጥቅም ላይ የሚውል ማንኛውም ዓይነት ዘዴ ነው፤

፰/ "የልህቀት ማዕከል" ማለት የቴክኖሎጂ ማመንጫ፣ መጠቀሚያ፣ ማስራጫና የዕውቀት ማበልፀጊያ ማዕከል ነው፤

፱/ "ሚኒስቴር" ማለት የግብርና ሚኒስቴር ነው፤

፲/ ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀው የሴትንም ይጨምራል፡፡

**መቋቋም**

፩/ ብሔራዊ የቆላ ዝንብና የገንዲ በሽታ መቆጣጠሪያና ማጥፊያ ኢንስቲትዩት (ከዚህ በኋላ "ኢንስቲትዩት" እየተባለ የሚጠራ) የህግ ሰውነት ያለው ራሱን የቻለ የፌደራል መንግሥት መስሪያ ቤት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡

፪/ ኢንስቲትዩቱ ተጠሪነቱ ለሚኒስቴሩ ይሆናል፡፡

**ዋና መሥሪያ ቤት**

የኢንስቲትዩቱ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በማናቸውም ስፍራ ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል፡፡

**ዓላማ**

የኢንስቲትዩቱ ዓላማ በቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ የተጠቁ የአገሪቷ አካባቢዎችን ከችግሩ ነፃ በማድረግ፣ የእንስሳትና የሰብል ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ እና ጥራቱን የጠበቀ የእንስሳት ምርት ለተጠቃሚ እንዲቀርብ በማድረግ ህብረተሰቡን በምግብ ራሱን በማስቻል ሂደት ተገቢውን አስተዋፆ ማድረግ ይሆናል፡፡



2/ "animal" means any domestic or wild animal:

3/ "trypanosomosis" means a disease caused by blood parasite;

4/ "parasite" means a single-celled blood parasite or protozoa that causes trypanosomosis;

5/ "trypanocidal drug" means an ingredient or a combination of ingredients used for treatment or prevention of trypanosomosis;

6/ "biological" includes reagents, tsetse fly species and animal blood used for laboratory examination and tsetse fly mass rearing;

7/ "technology" means any method used for control and eradication of tsetse fly and trypanosomosis;

8/ "center of excellence" means a center for technology production, application, dissemination and scaling-up of knowledge;

9/ "Ministry" means the Ministry of Agriculture;

10/ any expression in the masculine gender includes the feminine.

**3. Establishment**

1/ The National Institute for Control and Eradication of Tsetse Fly and Trypanosomosis (hereinafter the "Institute") is hereby established as an autonomous federal government organ having its own legal personality.

2/ The Institute shall be accountable to the Ministry.

**4. Head Office**

The head office of the Institute shall be in Addis Ababa and may have branch offices elsewhere, as may be necessary.

**5. Objective**

The objective of the Institute shall be to make areas affected by tsetse fly and trypanosomosis free of the problem with a view to increasing the products and productivity of animal and crops and providing animals of good quality to beneficiaries and thereby make proper contribution in the process of enabling the society to be self sufficient in food.

## ፮. ሥልጣንና ተግባር

ኢንስቲትዩቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩/ ለቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ቁጥጥርና ማጥፋት ስራ የሚያስፈልጉ ቴክኖሎጂዎችን ይለያል፣ ይገመግማል፣ ይመዝናል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፤ ችግር ፈቺ ጥናትና ምርምሮችን ያካሂዳል፤

፪/ ከቆላ ዝንብና ከገንዲ በሽታ ቁጥጥርና ማጥፋት ጋር በተያያዘ መመሪያዎችን ያወጣል፤

፫/ በቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ የተጠቁ አካባቢዎችን በመለየት ለስራ በሚያመች መልኩ ያደራጃል፤ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበርም ይሠራል፤

፬/ በቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ቁጥጥርና ማጥፋት ስራ የልህቀት ማዕከል በመሆን የአገር ውስጥና ዓለም አቀፍ ስልጠናዎችና የአቅም ማጎልበቻ መርሃ ግብሮችን ያዘጋጃል፤

፭/ ለቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ቁጥጥር የሚያስፈልጉ ኬሚካሎች፣ የላብራቶሪ ዕቃዎች፣ የመስክ መገልገያ ዎች፣ ቋሚ ዕቃዎችና አላቂ ዕቃዎች ስፔስፊኬሽን ያዘጋጃል፤

፮/ የአገልግሎት አሰጣጡን ለማቀላጠፍና ለማስፋፋት የሚረዱ ምቹ ሁኔታዎችን ይፈጥራል፤

፯/ በዘርፉ የተሻለ ልምድና ተሞክሮ ካላቸው የአገር ውስጥና ዓለም አቀፍ ተቋማት ጋር ጠንካራ ግንኙነት በመፍጠር አቅሙን ይገነባል፤

፰/ አሠራሩን ለማቀላጠፍና ለማጠናከር በቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ዘርፍ የተደረጉ አዳዲስ ሳይንሳዊ ግኝቶችን ከአገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማገና ዘብና በማጣጣም ጥቅም ላይ ያውላል፤

፱/ የቆላ ዝንብ፣ የገንዲ በሽታ፣ የሶሾ-ኢኮኖሚና አካባቢያዊ ሁኔታ መረጃ ይሰበስባል፤ መረጃውን መሰረት በማድረግ፡-

ሀ) የቁጥጥር ዘዴዎችና ስልቶችን ይለያል፣ ተግባ ራዊ ያደርጋል፣ ውጤቱን ይገመግማል፤

ለ) በዘርፉ የመረጃ ማዕከል ሆኖ ያገለግላል፣ የወቅታዊ መረጃዎች ተደራሽነትን ያረጋግጣል፤

ሐ) እንደአስፈላጊነቱ የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ መረጃዎችን ለባለሙያዎች፣ ለተመራማሪዎች፣ ለባለድርሻ አካላትና ለሌሎች ተጠቃሚዎች ያሰራጫል፤

፲/ ለእርባታና ለምርምር የሚሆኑ የቆላ ዝንቦችና ሌሎች ባዮሎጂካል ውጤቶችን የአገሪቱ ህግ በሚፈቅደው መሰረት ወደ አገር ውስጥ ያስገባል፣ ይጠቀማል፤ ወደ ውጭ አገርም ይልካል፤

## 6. Powers and Duties

The Institute shall have the powers and duties to:

1/ identify, review, evaluate and implement technologies that are necessary for control and eradication of tsetse fly and trypanosomosis; and conduct problem solving research and study;

2/ issue directives with respect to control and eradication of tsetse fly and trypanosomosis;

3/ identify areas affected by tsetse fly and trypanosomosis and organize them to make suitable for work, and work in collaboration with the relevant bodies;

4/ prepare national and international trainings and capacity building programs by becoming a center of excellence in relation to control and eradication of tsetse fly and trypanosomosis;

5/ prepare specifications for chemicals, laboratory materials, field equipments, fixed assets and consumables required for the control and eradication of tsetse fly and trypanosomosis;

6/ create conducive conditions that enhance the efficiency and expansion of its service delivery;

7/ build its capacity by creating strong relationship with national and international institutions that have best practice and experience in the field;

8/ apply new scientific findings in the field of tsetse fly and trypanosomosis by adapting them with the realities of the country to enhance its efficiency and to strengthen its systems;

9/ gather information with respect to tsetse fly, trypanosomosis, socio-economic and environmental conditions; and based on the information:

a) identify controlling mechanisms and strategies, apply same, evaluate the outcome;

b) serve as center of information, ensure accessibility to up-to-date information;

c) disseminate, as may be necessary, information in relation to tsetse fly and trypanosomosis to professionals, researchers, stakeholders and other users;

10/ import and use or export, in accordance with the country's laws, tsetse flies and other biological products for tsetse mass rearing and research;

፲፩/ የቆላ ዝንብ ዕርባታ፣ የጥራት ቁጥጥርና ምርምር በማካሄድ ብቁና ተወዳዳሪ የሆኑ ወንድ የቆላ ዝንቦችን ያመርታል፣ አምክኖ መስክ ላይ ይለቃል፣ ይከታተላል፤

፲፪/ ከቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ቁጥጥር ጋር በተያያዘ መስራት የሚፈልጉ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ሊሳተፉ የሚችሉበት መስፈርት ያዘጋጃል፤ በመስፈርቱ መሰረት እንዲሳተፉ ይፈቅዳል፣ ክትትልና ግምገማ ያደርጋል፤ ከመስፈርቱ ውጭ የሚሰሩትን ያግዳል፤

፲፫/ ለቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ቁጥጥር ወይም ለላብራቶሪ አገልግሎት የሚውሉ ኬሚካሎችና መድሃኒቶች የአገልግሎት ጊዜያቸው ከማብቃቱ በፊት ስራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፤ የአገልግሎት ጊዜያቸው ያለፈባቸውን ኬሚካሎችና መድሃኒቶች ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን እንዲወገዱ ያደርጋል፤

፲፬/ የንብረት ባለቤት ይሆናል፤ ውል ይዋዋላል፤ በራሱ ስም ይከሳል፤ ይከሰሳል፤

፲፭/ ዓላማውን ለማስፈፀም የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል።

፯. የኢንስቲትዩቱ አቋም

ኢንስቲትዩቱ፦

፩/ የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ቁጥጥርና ማጥፋት ስራዎች ምክር ቤት (ከዚህ በኋላ "ምክር ቤት" እየተባለ የሚጠራ)፤

፪/ በመንግስት የሚሾሙ ዋና ዳይሬክተርና እንደአስፈላጊነቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች፤ እና

፫/ አስፈላጊው ሠራተኞች፤

ይኖሩታል።

፰. የምክር ቤቱ አባላት

፩/ የምክር ቤቱ አባላት አግባብነት ካላቸው የመንግሥት መስሪያ ቤቶችና ከግሉ ዘርፍ የተወጣጡ ሆነው በመንግሥት ይሰየማሉ።

፪/ የምክር ቤቱ አባላት ቁጥር እንደአስፈላጊነቱ ይወሰናል።

፫/ የኢንስቲትዩቱ ዋና ዳይሬክተር ድምጽ የመስጠት መብት ሳይኖረው የምክር ቤቱ ጸሐፊ ሆኖ ያገለግላል።

፱. የምክር ቤቱ ሥልጣንና ተግባራት

ምክር ቤቱ፦

፩/ የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታን ለመቆጣጠርና ለማጥፋት እንዲቻል የቁጥጥርና ማጥፋት ስራዎችን ለመተግበር የሚያስፈልጉ በኢንስቲትዩቱ የሚዘጋጁ ስትራቴጂዎችንና እቅዶችን ይመረምራል፣ ያጸድቃል፤

11/ by conducting tsetse mass rearing, quality control and research, produce, irradiate and release efficient competitive male tsetse flies and monitor same;

12/ adopt criteria for allowing interested non-governmental bodies to participate in the control and eradication of tsetse fly and trypanosomosis; authorize their participation in accordance with the criteria, monitor their activities and suspend those acting in contravention of the criteria;

13/ follow up whether chemicals and trypanocidal drugs intended for control of tsetse fly and trypanosomosis or laboratory use are used before the dates of their expiry and, together with the concerned body, effect the disposal of expired chemicals and trypanocidal drugs;

14/ own property, enter into contract, sue and be sued in its own name;

15/ perform such other related activities that further its objective.

7. Organization of the Institute

The Institute shall have:

1/ Tsetse Fly and Trypanosomosis Control and Eradication Council (hereinafter the "Council");

2/ a Director General and, as may be necessary, Deputy Director Generals, to be appointed by the government; and

3/ the necessary staff.

8. Members of the Council

1/ Members of the Council shall be drawn from the appropriate government offices and the private sector and be appointed by the government.

2/ The number of members of the Council shall be determined as required.

3/ The Director General of the Institute shall serve as secretary of the Council without having the right to vote.

9. Powers and Duties of the Council

The Council shall:

1/ review and approve strategies and plans prepared by the Institute with a view to controlling and eradicating tsetse fly and trypanosomosis;

፪/ በኢንስቲትዩቱ የተዘጋጁ የአቅም ግንባታ መርሃግብሮችን ይመረምራል፣ ያጸድቃል፤

፫/ የኢንስቲትዩቱን እቅድ አፈጻጸም በየሶስት ወሩ ይገመግማል፣ የማስተካከያ አቅጣጫዎችን ያስቀምጣል፡፡

## ፲. የምክር ቤቱ ስብሰባዎች

፩/ ምክር ቤቱ በየሶስት ወሩ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል፤ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በማንኛውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል፡፡

፪/ ከምክር ቤቱ አባላት መካከል አብዛኞቹ በስብሰባው ላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል፡፡

፫/ የምክር ቤቱ ውሳኔዎች በድምጽ ብልጫ ያልፋሉ፤ ሆኖም ድምጽ እኩል በእኩል ከተከፈለ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል፡፡

፬/ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ምክር ቤቱ የራሱን የስብሰባ ሥነ ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

## ፲፩. የዋና ዳይሬክተሩ ሥልጣንና ተግባር

፩/ ዋና ዳይሬክተሩ የኢንስቲትዩቱ ዋና ስራ አስፈፃሚ በመሆን ከሚኒስቴሩ በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ መሠረት የኢንስቲትዩቱን ስራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል፡፡

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ፡-

ሀ) በዚህ ደንብ አንቀጽ ፯ የተመለከቱትን የኢንስቲትዩቱን ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል፤

ለ) የኢንስቲትዩቱን ድጋፍ ሰጭ ሠራተኞች በፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎች መሰረት እንዲሁም የኢንስቲትዩቱን ዓላማ በማስፈጸም ስራ ላይ የሚሰማሩ ባለሙያዎችን የፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎች መሰረታዊ መርሆዎችን ተከትሎ በመንግሥት በሚጸድቅ መመሪያ መሰረት ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፤

ሐ) የኢንስቲትዩቱን የስራ ፕሮግራምና በጀት ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድም በስራ ላይ ያውላል፤

መ) ለኢንስቲትዩቱ በተፈቀደው በጀት መሰረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤

ሠ) ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ኢንስቲትዩቱን ይወክላል፤

ረ) የኢንስቲትዩቱን የስራ አፈፃፀምና የሂሳብ ሪፖርቶች አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፡፡

2/ review and approve capacity building programs developed by the Institute;

3/ evaluate the implementation of plans of the Institute every three months and set directions for improvement.

## 10. Meetings of the Council

1/ The Council shall convene its ordinary meetings every three months; provided, however, that it may hold extraordinary meetings at any time as may be necessary.

2/ There shall be a quorum where the majority of the members of the Council are present at a meeting.

3/ The decision of the Council shall be passed by majority vote and, in the case of a tie, the Chairperson shall have a casting vote.

4/ Without prejudice to the provisions of this Article, the Council may adopt its own rules of procedure.

## 11. Powers and Duties of the Director General

1/ The Director General shall be the chief executive officer of the Institute and shall, subject to the general directions of the Ministry, direct and administer the activities of the Institute.

2/ Without limiting the generality stated under sub-article (1) of this Article, the Director General shall:

a) exercise the powers and duties of the Institute specified under Article 6 of this Regulation;

b) employ and administer employees engaged in support services of the Institute in accordance with the federal civil service laws and, in the case of employees engaged in the core functions of the Institute, in accordance with directives approved by the government following the basic principles of the federal civil service laws;

c) prepare the work programs and budgets of the Institute and implement same upon approval;

d) effect payments in accordance with the budget approved for the Institute;

e) represent the Institute in its dealings with third parties;

f) prepare and submit to the Ministry the performance and financial reports of the Institute.

፫/ ዋና ዳይሬክተሩ ለኢንስቲትዩቱ ስራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለኢንስቲትዩቱ ሌሎች ኃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡

**፲፪. <u>በጀት</u>**

የኢንስቲትዩቱ በጀት በመንግስት ይመደባል፡፡

**፲፫. <u>የሂሳብ መዛግብት</u>**

፩/ ኢንስቲትዩቱ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል፡፡

፪/ የኢንስቲትዩቱ የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም እርሱ በሚሰይ ማቸው ኦዲተሮች በየዓመቱ ይመረመራሉ፡፡

**፲፬. <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ የካቲት ፳ ቀን ፪ሺ፮ ዓ.ም

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

3/ The Director General may delegate part of his powers and duties to other officers and employees of the Institute to the extent necessary for the efficient performance of the activities of the Institute.

**12. <u>Budget</u>**

The budget of the Institute shall be allocated by the government.

**13. <u>Books of Accounts</u>**

1/ The Institute shall keep complete and accurate books of accounts.

2/ The books of accounts and financial documents of the Institute shall be audited annually by the Auditor General or by auditors designated by him.

**14. <u>Effective Date</u>**

This Regulation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

Done at Addis Ababa, this 27th day of February, 2014.

**HAILEMARIAM DESSALEGN**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**